ታኅሳስ 6 ቀን 2006

**ለተከበሩ የኢሣት (የኢትዮጵያ ሣተላይት ቴሌቪዥን) አዘጋጅ/Editor**

# ጉዳዩ፡- ቅሬታዬን ስለማሰማት፤

ከሁሉ አስቀድሜ ሰላምና ጤና ለተከበሩ የኢሣት አዘጋጅና የሥራ ባልደረቦችዎ እንዲሆንና አቤቱታዬም ከቀና ልቦናዎ እንዲደርስ ጸሎቴ ነው። ምናልባትም የአቤቱታዬ አቀራረብ ለጆሮዎ ጎርብጦ ካገኙት ወድጄ ሳይሆን ብሶት ስላለብኝ መሆኑን ከወዲሁ ላስገነዝብዎ እወዳለሁ።

አቤቱታዬን ሳስከትልም፣ "ጉድና ጅራት ከወደ ኋላ ነው" ብዬ ማመልከቻዬን ልጀምር ፈልጌ ነበረ፤ ግን ተውኩት። **ለምን? ለምንማ፣**

ሀ. "ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው" እሚባለው ስላለ - ጉዳችሁን፣ ጅራታችሁንም ዉሎ ከማደሩም በፊት፣ ከመጀመሪያዉኑ እናንተው ስለምታዉቁት፤

ለ. "ጉዱ የእኛ፤ ጅራቱም የእኛ" ብትሉኝ መልስ ስለሚያጥረኝ - "ዉሻ ምናገባሽ በሰው እርሻ?" እሚባለው እንዳይደርስብኝ እንጂማ ነው።

ይልቅስ፣ በእናንተው መሪ ቃል "ኢሣት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይንና ጆሮ" በሚለው መጀመሩን ፈቀድኩ። **በዚህስ ለምን?** በዚህስ ለምንማ፣ እማትሆኑትንና ልትሆኑም እማትችሉትን "ዓይንህም፣ ጆሮህም እኛ ነን" ስትሉኝ፤ "የለም፤ የለም፣ እንዴት ተሁኖ፤ ይኸው እዩታያችሁ - ዓይኖቼን እያጥፋችሁ፤ ምናምንቲያችሁን ሁሉ እያመጣችሁ ጆሮዎቼን እዩለገጣችሁ ኸረ፣ እንዴት ተሁኖ (ደግሜ ማለት እማልፈልገው መሪ ቃላችሁ) ልትሆኑኝ ትችላላችሁ?" ብል "ዉሻ ምናገባሽ በሰው እርሻ?" ልትሉኝ አያስኬዳችሁም።

ግን ለመሆኑ፣ ከሀቁ ጋር ያልተጣሉ ዓኖችና ጆሮዎች እናንተው ለእራሳችሁ አሏችሁን? - "እሚሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ!" እሚለው አባባላችን ባለሙያ እንደሰፋው ካፖርት ከእናንተ ጋር አቤት ልክክ ሲል። ታያችሁ አይደል?

መቼም፣ እስከ እዚህ ድረስ ባለው የአቤቱታዬ አካሄድ ሳይገባችሁ እንዳልቀረ ተስፋ አለኝ።

እኔ ከኢትዮጵ ሕዝብ አንዱ ነኝ። ደስታዬ ያገሬም ደስታዋ፣ ጉዳቴም ላገሬ ጉዳቷ ነው። ያገሬም ደስታዋ ለእኔ ደስታዬ፣ ጉዳቷ ለእኔም ጉዳቴ መሆኑን ጠንቅቄ እማዉቅ ዜጋ ነኝ።

ሌላም አለኝ። መንግስቱ በመራው የሰው በላው ሥርዓት ክፉኛ የተጎዳሁም አንድ ኢትዮጵያዊ ነኝ፤ በዚህም ኢትዮጵያ ተጎድቻለሁ ብላለች።

**ይህም ብቻ አልነበረም፣** የሥጋ ወንድሜን አሳጥቶኛል። ኢትዮጵያንም አጥታዋለች።

**ይህም ብቻ አልነበረም፣** የትግል እህቶቼንና ወንድሞቼን የዕድሜ ልክ የልብና የአካል ስብራት ያደረሰ መሆኑን አይቻለሁ፤ ኢትዮጵያም አካሏና ልቧ፣ መሰበሩ ተሰምቷቷል።

**ይህም ብቻ አልነበረም፣** የትግል እህቶቼንና ወንድሞቼን እስከ ወዲያኛው አሳጥቶኛል፤ ኢትዮጵያም አጥታቸዋለች።

**ይህም ብቻ አልነበረም፤** ወላጆች ልጆቻቸዉ ለተገደሉበት የጥይት ዋጋ ሲከሉ አዉቃለሁ፤ ኢትዮጵያም አዝናለች።

**ይህም ብቻ አልነበረም፤** ወላጆች አታልቅሱ ተብለዉ ሲደበደቡ፣ ሲታሰሩ፣ ሲገደሉ… አዉቃለሁ፤ ኢትዮጵያም ጉድ ብላለች።

**ይህም ብቻ አልነበረም፤** ከሃዲዉ መንግስቱ ኢትዮጵያን ለአገር አጥፊዎች አስረክቦ ሲኮበልል አይቻለሁ፡ ኢትዮጵያም የደም እንባ አፍሳለች።

**ይህም ብቻ አልነበረም፤** "ሳላዉቅ ነዉ፣ እንዳትመለስ ተብዬ ነዉ" ብሎ ከሃዲዉ መንግስቱ ሲዋሽ ሰምቼዋለሁ፤ ኢትዮጵያም ተሳልቃበታለች።

**ይህም ብቻ አይደለም፤** በአሜሪካንም እገዛ እንደ ኮበለለ አዉቂያለሁ፤ ኢትዮጵያም እርሚን አውጥታለች።

**ይህም ብቻ አልነበረም፤** ሰዎ-በላዉና የግራዚያኒ መንፈስ ዉላጅ የሆነዉ መግስቱ ስንትና ስንት ዶክተሮችንና ዶክተሮች ሊሆኑ ይችሉ የነበሩትን ታዳጊ ወጣቶች በጠራራ ፀሀይ የቀረጠፈ ቃላባዩ ፍጡር ልጆቹ ዶክተሮች ስለሆኑለት ደሰተኛ መሆኑን ካንደበቱ በሰማሁ ጊዜ ለቅሶዬን ደርድሪያለሁ። ኢትዮጵያም ኧረ፣ አሁንስ በዛ! ስትል ሰምቻለሁ።

እንዲህ፣ እንዲህ እያልኩ በእዚያ ክፉ ዘመን በፋሽስት ምርጥ መኮንኖች ቡድንና በአደግዳጊ ምሁራኖቻችን የተካሄደብንን ግፉና በደል ልዘርዝር ብል እስከወዲያኛዉም ቢሆን ግፉንና በደሉን ደርድሬ እንደ እንድማልዘልቀዉ እሙን ነዉ።

**እናም፣ ኢሳቶች!** ምን አርጉ ነዉ የምትሉን? ምንስ አርጊ ነዉ ኢትዮጵያን እምትሏት? ሰዎ-በላን ሁሉ፣ በሰዉ ዘር ማጥፋት እሚወነጀልን ሁሉ፣ ቃላባዩን ሁሉ፣ ካሃዲን ሁሉ፣ ፈርጣጭን ሁሉ… አፈላልጋችሁ እያመጣችሁ፤ ድምጻቸዉን እያሰማችሁ በቁስላችን ላይ ጨዉ የምትነሰንሱት? ኧረ፣ ከቶ ለምድን ነዉ? እዉን "የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይንና ጆሮ ነኝ" ከሚል ሚዲያ እሚጠበቅ ነዉን?

መግስቱስ፣ እስቲ እፍረት እሚባለዉ የሰዉ ባህሪ ያልተፈጠረበት ለመሆኑ መረጃ እሚያሳስብ ባለመሆኑ ልተዎዉ። አስተዛዛቢ ሆኖ ያገኘሁት "የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይንና ጆሮ" ሚዲያ ድፍረት ነዉ።

ኧረ፣ ከቶዉኑ ማን ይሆን፣ እንደዚህ እንድትደፍሩ የገፋችሁ - ያዉም ወራዳዉን መንግስቱ ኃለማሪያምን በሚዲያችሁ አቅርባችሁ በሰዉ አገር የነጻነት አርበኛ ኔልሰን ማዴላ ላይ እንዲሳለቅ ማድረጋችሁ? የእኛዎቹን ሰማዕቶቻችንን ማክቸልቸሉ አልበቃ አለና የሌላዉንም አገር የነጻነት ትግል ታሪክ ታራክሱት ገባችሁ። "ይቺ ሞት ተረማመደች" እንዳሉት እማሆይ ቀደም ቀደም አላችሁ።

**ኢሳቶች፣** እሰይ፣ እሰይ እንዲህ ነዉ እንጂ "'የእኛ ዓይንና ጆሮ' ሚዲያ - 'አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት የቄስ ሚስት፣ መጽሀፍት አጠበች' እንደዚህ ነዉ አይደል፣ ጎበዝ?" ብዬ እንድጠይቅም እዬገፋችሁኝ መሆኑን አስቡት።

**ኢሳቶች፣** ኧረ ተዉ፣ በዛ - ይድንበር ዘለላችሁ፤። "ሰልፋችን ከእነማን ጋር መሆኑን አያመላክትብንም" ብላችሁ ከሆነም እደተሸወዳችሁ እዎቁት! "ባናርስ እናጣምድ ነበር" እላችኋለሁ።

**እሣቶች፣** ብታዉቁማ መንግስቱ ከዚህ ግባ በማይባልበት ጊዜ ለደቡብ አፍሪካ ጥቁር ሕዝብ ድምጻቸዉን ያሰሙ የነበሩ የዚያ ትዉልድ አካሎች በህይወት አሉ እኮ። ምነዋ፣ እነ እርሱ

በዓይኖቻችሁ አልሞላ አለ? በትንንሽ ከተሞች እና በእዬ ገጠሩ የተበሉትን ሳንጨምር እንኳ አምስት መቶ ሺ ወገኖቻችንን የመተረ የደርግ/ኢሠፓ ቁንጮ “በእኛ ዓይንና ጆሮ” ሚዲያ ማቅረባችሁ? - ወይኔ አገሬ እንዲህ ሰዉ ይጥፋብሽ?።

ይህን ሳይሰሙ፣ ሳያዩ የሞቱት ጓዶቻችንና ቤተሰቦቻቸዉ ምንኛ ታድለዋል፣ ወገን?።

- ልብ በሉ! ኢሣቶች፣ የናዚ ሰዎች በእስራኤሎችና በዓለሙ በሙሉ እስካሁን ድረስ እዬተሳደዱ ነዉ - አይደለም ቃለ-ምልልስ እዬተደረጉ ሕዝብን አዳምጥ ማለት ቀርቶ።
- ልብ በሉ! ኢሣቶች፣ እስራኤሎች ጋዜጠኞች የሏቸዉምን? በዓለሙ ሁሉ ያሉ ጋዜጠኞች የጋዜጠኝነት ሙያ የሌላቸዉ ሆኖ ነዉን? በዲሞክራሲ ስለማያምኑ ነዉን? አይደለም እንድምትሉ በሙሉ ተስፋ ነዉ። እነ እርሱም እንደ እናንተዉ የሚዲያ ሰዎች ናቸዉ እኮ። ልዩነታችሁ፣ እነ እርሱ ሰዎ-በላን ሁሉ እንደ ናዚንና ሞሶሊኒ ሰዎች ዓይነቶችን አፈላልገዉ ድምጻቸዉን እያሰሙ የዜጎቻቸዉን ስሜት ሲፈታተኑ፣ ሎቦና ሲሰብሩ… አላዩሁም፤ አልሰማሁምም።
- ልብ በሉ! ኢሳቶች፣ እኔና ወገኖቼ ሁሉ በምናዋጣው ገንዘብ ነዉ መልሳችሁ ልብ ልባችንን እምታወልቁት።
- ልብ በሉ! ኢሳቶች፣ በአገሬ ልጆች ገንዘብ አገሬን የደም እንባ እያስለቀሳችኋት እንደሆነ።

በመጨረሻም፣ በዚህ እረገድ እሚመጣዉንና በሰማዕቶቼ ላይ እሚሳለቀዉን ማንም ይሁን ማን ከሰማዕቶቼ ጎን እሰከ እምወደቅባት ሰዓት ድረስ ከጓዶቼ ጋር ሆኘ፣ ሸንጧን ገትሬ እምታገለዉ መሆኑን ላስረግጥላችሁ ግድ ይለኛል።

ማመልከቻዬንም እንዲህ ቋጩሁት - የተከበሩ የኢሣት አዘጋጅ/Editor ማመልከቻዬን በጥሞና ዓይተዉ በፕሮግራሙ ስርጭት የተነሳ ለደረሰብኝ የስሜት ጉዳት ተገቢዉ ይቅርታ በኢሣት ፕሮግራም ሳይዉል ሳያድር እንዲተላለፍ፣ ወደፊትም እንዲህ ያለዉ የታዳሚን ስሜት እሚጎዳ ፕሮግራም ለአዬር ከማብቃት ኢሣት እንዲቆጠብ ክትትልዎ እንዳይለይ አበክሬ ሰብአዊነተዎን እሞግታለሁ።

በሉ! ኢሣቶች፣ ግፍ ፍሩ።
በሉ! ኢሣቶች፣ ልጅ እሚያወጣ ሥራ ስሩ።
በሉ! ኢሣቶች፣ ነገን አብረን እንድንቆም እንሁን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም በነጻነት ትኑር!
የሰማዕቶቻችን ደም እንበለ ፋይዳ ፈሶ አይቀርም!
በቁስሎቻችን ላይ ጨዉ እሚነሰንሱትንም እንፋረዳለን!

ከሳላምታ ጋር

ጃንተከል ተኳለ